# <u>የሰሜን አሜሪካ የእግር ኳስ ፌደሬሽን ባለስልጣናት</u>
# <u>በሕዝብ ላይ ቀለዱ ተባለ</u>

**የሰሜን አሜሪካ የእግር ኳስ ፌደረሽን ላይ ለዓመታት ብዙ ጥያቄዎች ሲቀርቡ ቢቆዩም ዘንድሮ ግን ባለስልጣኖቹ መረን ለቀው በሕዝብ ላይ ከፍተኛ ንቀትን በማሳየት ከወያኔ ጎን ተሰልፈዋል የሚል ክስ እየተስተጋባ ነው።**

**ለዚህ ምክንያት የሆነው ከወያኔ/ኢሕአዴግ ጋር በማበር የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ተፃርሮ የቆመውን ሼክ አላሙዲን ወዳጅ ብለው ገንዘብ መቀበላቸው ብቻ ሳይሆን የክብር እንግዳ አድርገው ለዋሺንግተኑ የዘንድሮ ውድድር ጋብዘውታል የሚል ዘገባ በመደመጡ ነው ተብሏል። ውድድሩ ትላንት ጁን 29 ሲከፈት በስታዲየሙ የክብር እንግዳ ሆኖ የተገኘው ግን የአላሙዲ ቀኝ እጅና ጉዳይ አስፈፃሚ የሆነው አብነት ገብረ መስቀል ነው። ለጊዜው አልሸሹም ዞር አሉ ቢሆንም አላሙዲ አሁንም ይመጣ ይሆናል ተብሎ በመጠበቅ ላይ ነው። አብነት የተባለው የአላሙዲ ሎሌ ስም ጥፉ የሆነ ባንዳ መሆኑም አውቃለን በሚሉ ተዘግቧል። የሴት ጓደኛዬ ላይ ቀናሁ ብሎ በአሜሪካ ሳለ አፍኖና አስሮ ፀጉሯን መላጨቱ ይጠቀሳል። አብነት ሆነ አላሙዲ በስታዲየሙ በመገኘታቸው በሰሜን አሜሪካ ውድድሩ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ጠንካራ የተቃውሞ እርምጃዎችን ይወስዳሉ ተብሎ ይጠበቃል። ምናልባትም ይህ ስራው መጥፎ እየሆነ የቀጠለውም ፌዴረሽን መለወጫው ጊዜ ደርሷልና ዜጎች በጉዳዩ መክረው እርምት እርምጃ ሊወስዱም ይገባል።**